# ዴሞክራሲያ

## የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

### ወሬ ለጠያቂ ገበጣ ለአዋቂ
### (የኢሕአፓ ረጅም ጉዞ)

አላውቅም ማለት አያስገድልም የተባለው ተዘንግቶ፥ ዛሬ የማያውቀው አዋቂ፤ ያልነበረው ተራኪ ሆኖ በተሰየመበት ወቅት፥ ሀቁ ይህ ነው ብሎ መናገሩ ብቻ ሳይሆን መደጋገሙ የግድ ሆኖ ይገኛል፡፡ ኢሕአፓ የአፍራሽና የሀሰት ፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ተጠቂ ሆኖ የቆየ ሲሆን፥ ዛሬ ከአጋር ድርጅቶች ጋር አብሮ በሠላማዊው መንገድ ለመታገል ወስኖ በኅበረት ግንባር በተሰለፈበት ወቅት፥ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ጋሬጣ እየዘረጋና በድርጅቱም ላይ አሉታዊ ዘመቻ እያካሄደ መሆኑን እያየን ነው፡፡ የእነ መለስ ነገር፥ ዋሽ ቢሉኝ እዋሻለሁ ነፉስ በወጥመድ እይዛለሁ ነውና በአሁኑ ጊዜ የከፈቱት ፀረ ኢሕአፓ ዘመቻ ታሪክንም ከልሶና በርዞ ከማቅረቡ ሌላ፥ ሀሰትን ሀቅ ብሎ ለማንገሥ የሚውገረገር ነው፡፡

የኢሕአፓና የወያኔ ቅራኔ በሥልጣን ሽሚያ፤ በገንዘብ ፍሊጋ ወይንም በአልባሌ ልዩነት የተከሰተ ሳይሆን፥ በሁለት ተቃራኒ ራዕዮች መሀል ብቅ ያለ መታረቅ ያቃተው ልዩነት ነው፡፡ በወያኔ ምሥረታ ሂደት፥ የሻዕቢያን ሚናና ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት በሚለው፥ በወያኔ በተደገፈውና በኢሕአፓ ተቀባይነት ባጣው የሻዕቢያ አቋም የተነሳውን ችግር ወደ ጎን ብንተው፥ ከምሥረታው ጀምሮ ወያኔ ከኢሕአፓ ጋር የተጋጨው በነበረው መሠረታዊ ፕሮግራሙ የተነሳ ወይም ባወጣው ማኒፌስቶ የተነሳ ነው፡፡ በዚሁ መሠረታዊ ሰነዱ ወይ መመሪያው፥ ወያኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ እርስ በርሱ በብሄረሰብ ቅራኔ ተቀይዶ በአንድነት መኖር ስለማይችል፥ ሁሉም ብሄረሰብ የየራሱን ነፃ ሬፓብሊክ/ ሀገር መመሥረት አለበት ብሎ ወያኔ በይፋ በመውጣቱ፥ ኢሕአፓ ወዲያውኑ ተቃወመ ፡፡ ትግላችን ፀረ አማራ ነው ያሉት እነ መለስ ዜናዊም የመጨረሻ ግባችን፥ ግንጠላን አስፍነን፥ ነፃ የትግራይ ሬፓብሊክን መመሥረት ነው ያሉትን ኢሕአፓ አጥብቆ ኮነነ ፡፡ ለመላ ኢትዮጵያ መታገል አኩሪና አስመስጋኝ ሆኖ ሳለ፥ የወያኔ መሪዎች ስጋ ቀርቦለት፥ ዓይኑ ወደ ፈርስ ዓይነት ሆነው ለውሱንና ጠባብ ዓላማ ማንሳታቸውን ኢሕአፓ አወገዘ ፡፡ ጭቁኑ አማራም ቢሆን ተረፍ መረፍ ወይም ትርፍራፊ ጨቋኝ ከተባሉት አግኝቷልና ጠላታችን ነው ያሉትን ኢሕአፓ ጠባብ ብሄርተኝነታቸውንና አፍራሽ ተግባራቸውን ወነጀለ ፡፡ ኢሕአፓ ለኢትዮጵያ፥ ወያኔ ለጠባብ ዓላማ ማለትም ለትግራይ መገንጠል በመሰለፋቸውና ሁለቱም የታጠቀ ኃይል በትግራይ በማሰመራታቸው፥ በሁለቱ ድርጅቶች መሀል ቅራኔው ተፋፋመ፡፡ አለንጋው እስኪመጣ በክርን አዝግሙብኝ እንደሚለው አሳፋሪ ፍጡር፥ ኢሕአፓ ላላመነበት እጅ መስጠት የለመደበት አልነበረምና ችግሩ እንደሚባባስበት ቢያውቅም፥ የሻዕቢያን የቅኝ ግዛት ትንተናም ሆነ የወያኔን ትግራይ በጠላት አማራ ተመዝብራለችና መገንጠል አለባት የሚለውን አቋም አልቀበልም ብሎ አሻፈረኝ አለ፡፡ አረምን መንቀል ስር ሳይሰድ ነው እንደሚባለው፥ ይህንን አደገኛ ጠባብ ብሐረተኛ ቡድን በዚያን ወቅት ከምድረ ትግራይ በኃይል ማስወገድ የሚችልበት ምቹ ሁኔታ የነበረ ቢሆንም፥ ይህን አላደረገም፡፡ ምክንያቱም፥ በትዕግስት አሳልፎ፥ በጋራ ጠላት ላይ በጋራ እንታገል፤ የሁሉም መብት ለሚከበርባት አንድ ኢትዮጵያ እንዋደቅ ብሎ በመወሰኑ ነበ

ር፡፡  ከዚህም አርቆ አስተዋይነት አቋም በመነሳት፥ ወያኔን ለድርድር ዘጠኝ ጊዜ ጋብዞ ቢሞ
ክርም፥ የሸዋ ትምክህተኛ፣ የአባይ (ትልቂቷ)ኢትዮጵያ አቀንቃኝ ከመባል ሌላ ያተረፈው አ
ልነበረም፡፡ ወያኔም በሻዕቢያ ተደግፎና ኢሕአፓ፥ በቀይ ሽብር ጥቃትም ሆነ  በመሳሪያ  ዕ
ጥረት የተወጠረበትን ጊዜ መርጦ ከትግራይ ከግዛቴ ውጡልኝ ሲል የነበረውን ህልም በኃይል
 እውን ለማድረግ እርምጃ ወሰደ ፡፡ በዚህም አላስፈላጊና ወያኔያዊ ጦርነት፥ በርካታ ህይወት
 ጠፋ ፡፡ የኢሕአፓና የወያኔ ቅራኔም በደም ተለውሶ ተባባሰ ፡፡

ኢሕአፓ ይሙት የገደለ በሚል ድርቅ ብሎ ቂምን አርግዞ ትግሉ ግድ የሚለውን እርምጃ
 ከመውሰድ አለመቆጠቡን፥ ከተዋጋው ከመኢሶን ጋርም ያደረገው ቅንጅት ምስክር ነውና ከ
ወያኔም ጋር ቢሆን ከትግራይ ጦርነትም በኋላ ቢሆን፥ ለማበርና የወያኔንም አቋም ለማረቅ ከ
መጣር ወደኋላ አላለም ነበር፡፡ ወያኔ ግን  ያበደች ጋለሞታ እናቷን ትመታ ሆኖበት በኢትዮ
ጵያ ላይ አፀያፊና ዘረኛ ዘመቻውን በመቀጠል፥ ኢሕአፓን በዋና ጠላትነት ፈርጆ ማጥፋት
ነው በሚል አምኖ በጎንደርም በፓርቲው ላይ ዘመተ ፡፡ የዚህ ያመረረ ፀረ ኢሕአፓ ዘመቻ
ማጠየቂያው፥ ኢሕአፓ የተደራጀና የበሰለ ኢትዮጵያዊና ሀገር ወዳድ ኃይል በመሆኑ እንጂ
ሌላ ምክንያት አልነበረውም፡፡ የወያኔ መሪዎች ከሶማሌም፣ ከሱዳንም፣ ከዐረብ ሀገሮችና ቅጥ
ረኛ ፈላጊ ከሆነ የማንም ባዕድ ኃይል ጋር በፀረ ኢትዮጵያ ሴራ ተካፋይ ለመሆን የዝግጁ ዝ
ግጁ ሆኖ ቅጥረኝነቱን በተግባር አስመሰከረ፡፡  ታዲያ፥የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፌ አልሰጥ
ም ብሎ ከቆመው ኢሕአፓ ጋር  በጠላትነት መፈራረጃቸው ጨርሶ አስደናቂ አልነበረም፡፡
ውሎ አድሮ ወያኔ በተራ ጮሌነት ራሱን ኢሕአዴግ በሚል ቅብዓ አርዮስ ሲያጠምቅ፥ በየዋ
ህነት ሊያምኑት የተነሱትንም፥ ኢሕአፓ በማስጠንቀቁ እነ መለስ ዜናዊ ቅጥ አምባሩ ጠፍቶ
ባቸው ይርበተበቱ እንደነበር የቅርብ ትዝታ ነው፡፡ በወቅቱ ራሳቸውን የአክራሪዋ አልባኒያ
ደቀመዛሙርት ነን ይሉ ነበርና፥ ኢሕአፓን፥ በአድሃሪነት፣ በከበርቴነት፣ በፀረ ጭቁን ሕዝብ
ነት ዘመቻቸው አወገዙት፡፡ መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ፥ በኢሕአፓ ላይ ያተኮሩት፥ ገበናቸውን
ከማወቁ በላይ በቆራጥነትም ስለሚያጋልጣቸውና ስለሚታገላቸውም ጭምር ነበር፡፡ ኢሕአፓ
 ከወያኔም ከሻዕቢያም ተቃርኖ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ከደርግም ሽብርና ጥቃት ጋር እየታገለ
ባለበት ወቅት፥አይዞህ በርታ ያላሉትና አልፎም ለወያኔ ወይ ለደርግ ድጋፍ ሲሰጡ የነበሩት
፥ ዛሬ በተገላቢጦሽ የኢሕአፓን ኢትዮጵያዊነትና ሀገር ወዳድነት በጥያቄ ሊያስገቡ ሲጥሩ እ
የታዘብን ነው፡፡

ዛሬም ቢሆን መለስ ዜናዊና ግብረ-አበሮቹ ድርጅቱን በህገ-ወጥነት ፈርጀው የሚያሳድ
ዱትና በሠላም እታገላለሁ ሲልም ጋሬጣ የሚዘረጉበት፥ ኢሕአፓን ስለሚፈሩም ስለሚጠሉ
ም ነው፡፡ ስለሚጠሉት ስንል፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ስለሚጠሉና ሀገሪቷንም ለማውደም ስለ
ተነሱ፥ ብሎም ኢሕአፓም ኢትዮጵያዊ በመሆኑና ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም እየተሰዋ የ
ሚታገል ፓርቲ በመሆኑም ጭምር ነው፡፡ እነመለስ ዜናዊ ደግሞ ከሁሉም በላይ አምርረው
የሚጠሉትና የሚፈሩት ለኢትዮጵያ ስትራተጂያዊና ብሔራዊ ጥቅም የቆመውን ኃይል ብቻ
 ነው፡፡  ይኸ ባይሆን ኖሮ፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ አንጡራ ኃብት የተደራጀውን፥  የተገነባውን
 ተቋም ሁሉ ባላፈረሱትም ነበር፡፡ የወያኔ መሪዎች ኢሕአፓን እየፈሩ የሚጠሉትም ከዚህ አ
ኳያ  ስለሚቃወማቸው ነው፡፡

ኢሕአፓ፥ በገንዘብ፣ በሹመትም  ሆነ በጊዚያዊ ጥቅም ስለማይገዛ፥ በብሄረሰብ ደረጃ ስለ
ማይከፋፈልና ትምክህትንም ሆነ ጥበትን ስለማይቀበል፥ በኢትዮጵያ አንድነት ላይም ሆነ በ
ኢትዮጵያዊነቱ ስልማይደራደር፥  የወያኔን ገበናና ወንጀል ሳይታክት ስለሚያጋልጥ፥ መለስ
ና ግብረ-አበሮቹ ቢጠሉትና ቢፈሩት አይፈረድባቸውም፡፡  በረሀቡ ወቅት ከአሜሪካና ከሱዳን
 ተመሳጥረው የትግራይን ሕዝብ ለዕልቂት ዳርገው የንዋይና ሌላም ትርፍ እንዳካበቱ ስላጋለ
ጣቸው የኢሕአፓ ስም እንደ ኮሶ ያንገፈግፋቸዋል፡፡ ከዚያድ ባሬ ከሶማሊያ ጋር፣ ከኒሜሪ ከ
ሱዳን ጋር፣ ከግብፅ ጋር፣ ከሳውዲና ሊቢያ ጋር፣ ከአሜሪካና ከእንግሊዝ ጋር በፀረ ኢትዮጵያ
 ልዩ ልዩ ሴራዎች መሳተፋቸውን ስላጋለጠባቸው፥ኢሕአፓን እንደ አባታቸው ገዳይ ይቆጥ
ሩቷል፡፡   በመርህ አቋሙ  ላይ ወለም ዘለም ስለማይልና የከይሲ ዓላማቸው ፀር በመሆኑ  ኢ

ሕአፓና እኛ አጥፊና ጠፊ ነን ብለው ይቃዣሉ። ስለሚፈሩት ስንል፥ በድርጅት ብስለትና
አሰራር ስለሚበልጣቸው፥ ችሎታ ያላቸው አያሌ አባላት ያሉት ድርጅት በመሆኑና በአመ
ራር እርከን ያልገቡ አባሎቹ እንኳን ሲከዱ፥ ከመቅፅብት የወያኔ ዋና ሚኒስቴር መሆናቸው
የእነ መለስን ሰው አልባነት አጋላጭ በመሆኑ ነው። ከሁሉም በላይ ግን፥ ኢሕአፓ የሕዝብ
ድጋፍ ያለው ድርጅት በመሆኑ በፀረ ሕዝቦቹ ይፈራል። ሀሰተኛ በቃሉ፥ ስደተኛ በቅሉ ይ
ታወቃሉ ነውና፥ እነ መለስ ነጋ ጠባ ኢሕአፓ አብቅቶለታል፤ ፈርሷል፤ተሰዷል ወዘተ ብለ
ው ቢቀጥፉም፥ ዋሾ ውሸቱን ለማመን አይገደድምና፥ የራሳቸውን ቅጥፈት   ሀቅ ብለው አ
ልተቀበሉትም። ኢሕአፓ ከሕዝብ ትግልና ታሪክ ጋር የተቆራኘና ስሙ በማንም ሊፋቅ የማ
ይችል መሆኑን ያውቁታል። ሕዝብም ልጆቹን ለኢሕአፓ ዓላማ የገበረው፥ ዓላማው የራሱ
መሆኑን አምኖበት መሆኑ የሚያከራክር አይደለምና በወንጀል ከረከሰውና ከእበላ ባዩ የወያኔ
ሎሌ ባሻገር፥ ሕዝብ እንደ ሕዝብ ለኢሕአፓ በጎና ቀና አመለካከት እንዳለው እነ መለስ ያ
ውቃሉ። ለዚህም ነው ድርጅቱን በመፍራት ሊያገልሉትና ሊገድሉት ቀን ተሌት ፣ ትላንት
ም ዛሬም ሲራወጡ የሚታዩት። ወደ አዲስ አበባ ሥልጣን ለመያዝ በባዕዳን ተደግፈው ሲገ
ሰግሱ፥ በኢሕአፓ ላይ ጦርነት ከፍተውና ከሱዳን ጋርም አቀናጅተው ድርጅቱን ለማጥፋት
ባላቸው ኃይል ተንቀሳቀሱ። ድርጅቱ በለንደኑ የሰላም ተብዬ ጉባዔ እንዳይሳተፍም ጦር የለ
ውምና አያስፈልግም ብለው ዋሽተው አገዱ፤አሳገዱ። በአዲስ አበባው የሽግግር ጉባዔ እንዳ
ይሳተፍ ደግሞ ጦር አውጆ እየወጋን ነውና ለሠላማዊ ትግል ዝግጁ አይደለም ብለው በሩን
ዘጉ። ዋናው ዓላማቸው ኢሕአፓን ስለሚፈሩት፥ ማራቅ ማግለል፤ ማጥቃት ከቻሉም ማጥፋ
ት እንደሆነ የታወቀ ነው።

መለስ ዜናዊና ጭፍሮቹ ኢሕአፓን በጦረኝነት ሳያፍሩ ቢወነጅሉም ከ 1983 ዓ.ም. ጀም
ሮ ኢሕአፓ በሠላማዊ መንገድ ህጋዊ ሆኖ ለመታገል ያለውን ፍላጎት በተደጋጋሚ ገልጦ ነበ
ር። ባዕዳን በአዘጋጁቸው የድርድር መድረክ ሆነ፥ ኢትዮጵያውያን ራሳቸው በጀመሯቸው የ
ዕርቅና የሰላም ጥረቶች ግንባር ቀደም በመሆን፥ የበኩሉን አስተዋፅዖ አድርጓል። ለግዮን ሆ
ቴሉም ጉባዔ አባሎቹን ልኮ የገቡት በእነ መለስ መታሰራቸው የሚታወስ ነው። የዴሞክራሲ
መብቶች ከተከበሩና ኢሕአፓ በዚሁ መንገድ መብቱ ተከብሮ ከታገለ፥ እነ መለስን በምር
ጫ ለማሸነፍ መቻሉን ያምናልና ሰላማዊና ህጋዊ ትግልን በዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ፈርቶም ሸ
ሽቶም የሚያውቅ አይደለም። በቅርቡ በተቋቋመው የኢትዮጵያ የዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅ
ብረት አማካኝነትም፥ በሠላማዊ መንገድ ለመታገልና የነፃ ምርጫም ዓለም አቀፍ ቅድመ ሁ
ኔታዎች ከተሟሉ ከአጋር ድርጅቶች በጋራ በዚሁ ለመሳተፍ፥ መወሰኑን አስታውቋል። ይህ
ንን አቋሙን፥ የመለስ መንጋ መቀበል ስላቃተውና ኢሕአፓን ማግለል፤ መነጠልና ህገወጥ
በሚል ፈርጆ ማጥቃት በሚል መመሪያ የሚንቀሳቀሰው ዘረኛ ቡድን፥ ልዩ ልዩ እንቅፋቶች
ን እየወረወረ ኢሕአፓ በምስጢር ሳይሆን በይፋ በአደባባይ በሕዝብ መሀል ሊንቀሳቀስ እንዳ
ይችል እገዳውን ለማራዘም እየጣረ ነው። ይህ ሁሉ መቅበዝበዝ፥ የመለስ ቡድን ምንኛ ኢሕ
አፖን እንደሚፈራ የሚያመለክት ነው። ይህንን ፍራቻውን የሚጋሩና፥ ያፈሰሱት የንፁህን
ደም ዕረፍት የነሳቸው ደግሞ፥ ከመምህሩ ደቀመዝሙሩ እንዲሉ፥ ከወያኔ መሪዎች ባላነሰ ደ
ረጃ በኢሕአፓ ላይ አላግባብ ሲዘምቱ መታዘብ የግድ ሆኖብናል።

ከመለስ ዜናዊ ቡድንም ሆነ ከመሰል ክፍሎች፥ ኢሕአፓ ያለው መሠረታዊ ቅራኔ ሀገር
ና ሕዝብን የሚመለከት ነው። ኢሕአፓ የብሄረሰቦችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት
እስከመገንጠል ከሚለው ጋር ማወቁና መደገፉ ለሕዝብ መቀራረብና አንድነትን ለመምረጥ
ይጠቅማል በሚል ድምዳሜ ያመነበት ወቅት ቢኖርም፥ ይህንን በጠባቡ ተርጉመውና መገን
ጠል ወይ ሞት ብለው የተነሱ ብሄርተኛ ድርጅቶችን ሲያይ፥ አቋሙን በማረም መብትን ለ
ማረጋጋጥ ግንጠላን የመብቱ አጃቢ ማድረጉ የግድ አይደለም ብሎ ፕሮግራሙንም አስተካክ
ሏል። ከመጀመሪያውም ቢሆን፤ ኢሕአፓ ከወያኔ ጋር ግጭትና ቅራኔ ሲገባም ከ1967 ዓም
ጀምሮ ቢሆን፤ ሙሉ መብትን ማወቅ ይገባል ካለበት ጊዜም ሆነ፥ ከዚያም በፊት ቢሆን ፥ የ
ሕዝብ መብት የተከበረባት አንድ ኢትዮጲያ በሚል ታገለ እንጂ፥ ዛሬ አንዳንድ ሙያተኛ
ቀጣፊዎች እንደሚሉት ሀገር ትገነጣጠል ብሎ መቸም አቋም ወስዶ አያውቅም። በተቃራኒ
ው እንዲያውም፥ የሀገርን ጥቅም እንደ ወያኔ ለባዕድ አሳልፎ ለመስጠት ባለመዘጋጀቱና ሀገ

ርን ባለመካዱ የኢትዮጵያን ጥፋት የሚመኙ ክፍሎች ወያኔን አጋር ኢሕአፓን ሰይጣን ብለው ፈርጀው መከራ አሳይተውታል:: ኢትዮጵያን በተመለከተ ወያኔ ለግንጠላና ክፍፍል፥ ኢሕአፓ ደግሞ በዴሞክራሲ የሕዝብ አንድነት ለሚረጋገጥባት ኢትዮጵያ በመቆማቸውና በዚህም በመቃረናቸው ሆድና ጀርባ ሆነው ቆዩ:: በዚሁ በሀገር አንድነት ጥያቄ ላይም፥ ኢሕአፓ የተጨቆኑ ብሄረሰቦች መብት መከበር አለበት ብሎ ከትምክህትም ጋር በመቃረኑ የጭቆናውን ሥርዓት አዳናቂዎችና ሌሎችን ረግጦ በመግዛት ሀገርን እናስከብራለን/እናቀናለን ባዮች ጋርም የማይታረቅ የራዕይ ልዩነት እንዳለው ቀጥሏል::

ትላንትም ሆነ ዛሬ- ነገም ሆነ ምንጊዜም ፥ ኢሕአፓ፥ የኢትዮጵያ ነፃነት፥ የዜጎቿ እኩልነት፥ የሀገሪቱ ሠላም፥ የሕዝቧ ብልፅግናም ሆነ ልማትና ዕድገት የሚሳካው፥ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የሕዝብ ልዕልናና የህግ የበላይነት ሲረጋገጥ ብቻ ነው ብሎ ያምናል:: ይህ መሠረታዊ ሀቅ ለሀገራችን ኅልውና አልፋና ኦሜጋ ነው:: ይህንን መቀበልና ዕውን የሚሆንበት ሂደት ማምጣት አንገብጋቢና ወሳኝ መሆኑ አያከራክርም:: ከወያኔ መሪዎችም ጋር ያለያየን ይህ መሠረታዊ ግንዛቤ ነው:: የሀገር ሉዓላዊነትንም በተመለከተ ቢሆን፥ ገበያው በደራበት እናቱንም ሊያስማማ ከተነሳው ከከሀዲው የመለስ ቡድን ጋር፥ ኢሕአፓ የነበረውና ያለው ቅራኔ መሠራታዊ ነው:: መለስና ጭፍሮቹ ኢትዮጵያን ለባዕድ ጠላቶች ለመሸጥ አይናቸውን አላሹም:: አሜሪካንና ሱዳንን ለማስደሰት ሲሉ፥ በረሀብ የተጠቃውን የትግራይን ሕዝብ ለወዲ ከውሊና ለሱዳን የሞት መንደሮች ዳርገዋል:: ከሻዕቢያ ጥቅም ለማግኘት ሲሉም፥ ወጣት የትግራይን ልጆች ለሞት ዳርገዋል:: ሱዳንን ደስ ይበለው ብለው፥ የመተማንና የሁመራን ደንና ቅርቀሃ መጨፍጨፍ ብቻ ሳይሆን፥ የተከዜን ድልድይ ለማፍረስም ሞክረዋል:: የደቡብ ሱዳን ስደተኞችን እያፈሱ ለሱዳን ባለሥልጣኖች በማስረከብም በየእርሻው (መሽሩኡ) አሰረሽነዋል:: የተቸገረን የትግራይ ስደተኛ በሱዳን ሀብታም ባለእርሻ አስበዝብዘዋል:: ወጣት ስደተኛ ሴቶችን ለፖለቲካ ጥቅም ሲሉም ለሱዳን ባለሥልጣናት መጫወቻ አድርገዋቸዋል:: አልፈውም ለሊቢያው ገዳፊ አረብ ነን ብለው ጭራቸውን ቆልተዋል። አሳፋሪው መለስም፥ ዜናዊ የዐረብ ስም ነው፤ ኢትዮጵያም ወደ ዐረብ ሊግ ትገባለች፥ ብሎ ራሱ ዋሽቶና በፊልምም ተቀርጾ ሀገርን ለቅሌት አጋልጧል:: ኢሕአፓ በዚህ ሁሉ ወያኔን ተፃርሮና አጋልጦ፥ በተለይም ለባዕድ ሎሌነት ራሱን ባለማጨቱ ከወያኔ በተለይ ጎዳና ተጉዟል:: የደርግና የወያኔ የሀሰት ሹምባሾች ሌላ ቢሉም፥ ኢሕአፓ ለሱዳንም ሆነ ለሶማሊያ፤ ለማንም ባዕድ፥ ለድርጅታዊ ጥቅም ሲል መርኁን ሽጦ የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፎ አልሰጠም:: ያማ ቢሆን ኖሮ፥የምንሊክን ግቢ፥ ከመለስ በፊት እርሱ በያዘው ነበር:: በኢሕአፓ ዕምነትም ሆነ ዓላማ ፥ የሀገርን ብሔራዊ ጥቅም አሳልፎ በመሸጥና ዘለዓለም አብሮ የኖረን ሕዝብ በታትኖ የሚመጣ ሥልጣን ከነግሳንግሱ እንጦሮጦስ መግባት አለበት ይላል:: ለዚህም ነው፥ ኢሕአፓ፥ የባዕዳንን ሴራ እያጋለጠ ፤ የቅርብ ሀገሮች መንግስታትን ተንኮል እያወገዘ ፤ እነ እንግሊዝ፤ ኖርዌይ፤ ጀርመንና ሌሎችም ኢትዮጵያን ለመከፋፈልና ለማዳከም እያካሄዱ ያሉትን ሁሉ እየተዋጋ፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ተማምኖ መከራን ተጋፍጦ የቀጠለ ድርጅት የሆነው:: ኢሕአፓ እንደ ወያኔ ኢትዮጵያን ቢክድ ኖሮ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች፥ አቅፈውና ደግፈው ለቤተ መንግሥትና አሁን ወያኔ ላለበት ቦታ ባበቁት ነበር:: እምባጮው ወያኔ፥ የተቆረጠው ዝግባው እምቢኝ ስላለ ነበር እንጂ፥ በወያኔ ችሎታም ሆነ ብስለት፥ የጡት አባቶቹም ቢሆኑ እምነት አልነበራቸውም:: ዛሬም ቢሆን ኢሕአፓን ከሌሎች የሚለየው ዋናው ነጥብ ይኸው የሀገር ሉዓላዊነት ጉዳይ ነው::

የኢሕአፓን ሀገር ወዳድነትና ሕዝባዊ ፍቅርም ሆነ አርበኝነት ማንም ከጥያቄ ወስጥ ሊያገባው የሚችል የሞራል የበላይነት ያለው ኃይል የለም ብለው ከልባቸው ስለሚያምኑ፥ ከሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች የመጡት አባላቱ፥ የሀገር ወዳድነታቸውን ጉዳይ ከሁሉ በላይ ቅድሚያና አፅንዖት ይሰጡታል:: ለዚህም ነው፥ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ብሔራዊ ጥቅም ቀናዒ የሆኑት:: ወደፊትም ቢሆን፥ ይህ መሠረታዊ አቋማቸው አልፋና ኦሜጋ ሆኖ ይኖራል፥ ከዘለዓለማዊቷ ኢትዮጵያ ሀገራቸው ጋር! ይህ ጊዜ የማይሽረው የኢሕአፓ የፀና አቋም፥ ከነመለስ ዜናዊ ጋር ምን ጊዜም ቢሆን የሚጣጣም አይሆንም:: ይህም ሰብዕናው ይመስናል ኢሕአፓን፥ ኢትዮጵያዊ ትህትና በተላበሰ ኩራት ተጎናጽፎ እንዲታገል ብርታቱን የሰ

ጠው፡፡ ይህ ነው እንግዲህ በነመለስና የውጭ ጌቶቻቸው ዘንድ ጥርስ ውስጥ እንዲገባ ያደረገ
ው፡፡ ነገር ግን፥ እንኳን በጥርሳቸው በመጋዝም ቢከረክሩት ኢሕአፓ እንደሆን የሀገሩን ብሔ
ራዊ ጥቅም አስመልክቶ ፍንክች አይልላቸውም፡፡

ምን ጊዜም ቢሆን ኢሕአፓ ያለንበትን ዓለም አቀፍ ሁኔታ በጥንቃቄና በሚገባው መንገድ
የሚያጤን ነውና፥ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኃይሎችን አሰላላፍ ያውቃል፡፡ ወርቅን ለማግኘት
ወርቅ ይዞ መነሳት ቢባልም ግን ይህችን ታሪካዊ ሀገር ለባዕድ አሳልፎ በመስጠት የሚገኝ ጊዘ
ያዊ ጥቅምን ማሳደድ ህሊናውና መርሁ ዛሬም አይፈቅድለትም፡፡ ሌሎች ግን ታክቲክ በሚ
ል ሽፋን፤ ዘዴኛነት በሚል መመፃደቂያ፤ አቅምን አውቆ መኖር ችሎታ ነው በሚል የመሸታ
ቤት ግጥም መሠረት ወዘተ ራሳቸውን፤ ድርጅታቸውንና አልፎም ሀገርን ለባዕድ አሳልፎ በ
መስጠት ለሥልጣን ሲሯሯጡ እናያለን፡፡ ሥልጣን እንጂ ሉዓላዊነት ወይም የሀገር ክብር አ
ይታያቸውም፡፡ በደርግ ዘመን ለምሳሌ ኢሕዴአ ይባል የነበረ ቡድን ሚናው ይህ ዓይነት ነበ
ር፡፡ ዛሬም፥ ያለው አንድ ልዕለ ኃያል ብቻ ስለሆነ፥ ተወደደም ተጠላ ለእርሱ መንበርከክ
ግዳጃችን ነው የሚሉ አሳፋሪ ፍጡሮች ድርጅት ነን ብለው ተነስተዋል፡፡ በዘመኑ፥ ኃያል ለ
ነበረችው ጣሊያን እጅ አንሰጥም በማለት አይከፍሉ መሥዋዕት በመክፈል ሀገራችንን ከቅ
ኝ ግዛት ነፃ አውጥተው ባቆዩልን አርበኞች እግር የተተኩት አሳፋሪ ክፍሎች፥ ዛሬ ሕዝብ
ን ንቀው፥ ለባዕድ ገዥዎቻቸው እየሰገዱ መሆናቸውንም እያየን እየታዘብን ለመኖር ተገድ
ደናል፡፡ እነዚህም ጉዶኞች ኢሕአፓን በጠላትነት ፈርጀው የሚያጠቁት ናቸው፡፡ ታማኝ ተ
ቃዋሚ፤ የባዕድ ባልሥልጣን፥ ጎበዝ ልጆች/ሎሌዎች እንዲላቸው፥ የቡችላ ጭራቸውን የሚ
ቆሉ እነዚህ ክፍሎች፥ የሀገርን ሉዓላዊነት ለማንም አሳልፎ መስጠት የለበትም ከሚለው ኢ
ሕአፓ ጋር መሠረታዊ የራዕይ ቅራኔ አላቸው፡፡ ወደ ስረ መሠረቱ እንሂድ ካልን ደግሞ፥ ኢ
ሕአፓን ከእነ መለስ ዜናዊና ግብረ-አበሮቹ የሚለየው የፖለቲካ ሥልጣን ጉዳይ ነው፡፡ መለ
ስና መሰሎቹ ራሳቸውን፥ አለሁ ላለ ዲያብሎስ/ ለሰይጣን አሳልፈው ሰጥተውና ህሊናቸውን
ም ሸጠው፥ ወይ ሀገር ወዳድነትን ገድለው፥ የሰው ሀገሩ ሆዱ በሚል መርህ ባለሥልጣን መ
ሆን ይፈልጋሉ፡፡ መለስ ዜናዊ ይሾመናል በሚል፥ የሕዝብን ትግልና ኅብረት ሲያዳክሙ እያ
የን ነው፡፡ ኢሕአፓ በበኩሉ፥ የፖለቲካ ትግል ዓላማው፥ የፖለቲካ ሥልጣን መሆኑን ቢያ
ውቅም፥ ይህ ሥልጣን የሕዝብን መብትና የሀገርን ሉዓላዊነት እስካላስከበረ ድረስ፥ በአፍን
ጫየ ይውጣ ባይ ነው፡፡ ስለዚህም፥ ኢሕአፓ የደርግም የወያኔም ሹመት አንጉቶት ወይም የ
ወያኔ የይስሙላ ፓርላማ ተመራጭ አባል ለመሆን ወዘተ ሲል ሀገሩን፤ ወገኑንና መርኑን አሳ
ልፎ ለመስጠት ፍፁም ዝግጁ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ወደፊትም የሚያደርገው ቀርቶ የሚያስበ
ውም አይሆንም፡፡ የመከራ ሌሊት የማያልቅ ቢመስልም፥ የኢሕአፓ ሀቀኛ አባላት ሰለቸን
መረረን ብለው ሀገራቸውን፤ ወገናቸውንና ብዙዎች ሰማዕታት ጓዶቻቸው የወደቁለትን የተ
ቀደሰ ዓላማ እንደ ወያኔ ለመሸጥ ዝግጁ አይደሉም፡፡ ከወያኔዎቹ ጋርም በመሠረቱ የሚለያ
ቸው አንዱ ይኸ ባኅርያቸውና ሰብዕናቸው ነው፡፡ የኢትዮጵያን ባኅርይ፥ ሰብዕናና መስተጋ
ብር አንግቦ የሚታገል ድርጅት፥ የመጨረሻው አሸናፊ እንደሚሆን ደግሞ ጭራሽ ብዥታ
ሊኖር አይችልም፡፡

ኢሕአፓ መተከላዊ አቋሜና ዕምነቴ ሕዝባዊ ነው ሲል፥ በሃቅ እንጂ ለሕዝብ ቆመናል
እያሉ በሕዝብ መብት ላይ እንደሚፈነጩት እንደነ መለስ ባለመሆኑ፥ ከእነርሱ ተፃርሮና ከ
ሕዝብ ጎራ ወግኖ ይታያል፡፡ ነፃ አውጪዎች ነን ብለው ተሞካሽተው፥ ግን ሕዘቡን ራሱን
በመከራ የጠበሱትና ያሰቃዩት እነ ወያኔ ማንና ምን እንደሆኑ፥ ቀደም ሲል የትግራይና የጎ
ንደር ሕዝብ፥ ውሎ አድሮ ደግሞ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያውቀው ነው፡፡ ይህ ደግ
ሞ፥ ኢሕአፓ ከነበረውና ካለው ንፁህ የሕዝብ ፍቅር በጣም የተለየና የተቃረነ ነው፡፡ ኢሕ
አፓ የምርጦች አስተሳሰብንና አገዛዝን፤ ተምረናልና ከሕዝብ እንበልጣለን፤ ከተሜ ነንና ከባ
ላገሩ እንሻላለን፥ ከወርቅ ዘር ተወልድንን እንጂ፥ ከጨርቅ ዘር አልመጣንምን ዓይነት አድሃሪ
ና አሳፋሪ ፀረ ሕዝብ አቋሞችንና አስተሳሰቦችን ተቃውሟል፤ ታግሏል፡፡ ዛሬም እየታገለ ነው፡
፡ የኢሕአፓ ሕዝባዊነት የይስሙላ አይደለም፡፡ ጭቁን ሕዝብ፤ ሰርቶ አደሩ ሕዝብ የሥልጣን
ባለቤት ይሁን ሲል፥ በዚህ ስምና ሽፋን መንግሥቱም ሆነ መለስ፥ ሌሎቹም አረመኔዎች
ሥልጣን ይጨብጡ ማለቱ አይደለም፡፡ ተማርን የሚሉ ከተሜዎችም ባልሥልጣን ሆነው ከ

ተሜውንም ሆነ ገጠሬውን ሰፊ ሕዝብ ጭምር ይንገሡበት፤ ይጫወቱበት ይፈንጩበት ማለ
ቱም አይደለም። ሕዝብ የሥልጣን ባላቤት ይሁን ብሎ ኢሕአፓ ሲሟገትም፥ በዚህም የተነ
ሳ ከእነ መለስና መሰል አምባገነናዊ ቢድኖች ጋር ሲጋጭ፥ የሕዝብ መሠረታዊ መብቶች፥
ያለገደብ ተከብረው፥ ድህው፥ ሠርቶ አደሩ ሕዝብ በሞላ፥ በሀገሩ ባለመብት ዜጋ ሆኖ፤ በነገ
ይዘት ላይ ወሳኝ ሚና ኖሮት፤ ሳይፈራ፥ ሳይሸማቀቅ፤ በሁለተኛ ደረጃ ዜጋነት ሳይመደብ፤
በብሄረሰቡ ፤ በሃይማኖቱና በፆታው አድልዖ ሳያጋጥመው፥ ኩሩና ባለመብት ኢትዮጵያዊ ሆ
ኖ የሚኖርበትን ሁኔታ እውን ይሁን ለማለት ነው። በዛሬይቷ ኢትዮጵያ ወርቅ ዜጋና ጨርቅ
ዜጋ አለ ። ለትምህርት ያልታደሉ ጎፃናት፥ ሠርቶ ለመብላት ያልቻሉ ወጣቶች አደገኛ በዘ
ኔ በሚል አሳፋሪ ፈሊጥ ዕድላቸው ውኑኒ መወርወር ሆኗል። ብዙኃኑ ይራባል፤ ጥቂቶች ደ
ግሞ ባለጌ በሚባል ደረጃ ይንደላቀቃሉ። ፍትህ ርትዕ ደብዛዋ ጠፍቷል። ህፃናት መንገድ አ
ዳሪና የስቃይ ሰለባ ሆነዋል። ጥቂቶች ደግሞ በአስረሽ ምቺው ደንዘው ልጆቻቸውንም አንደ
ላቅቀው፥ ድሃ ማለት ምንድ ነው? እስከ ማለት ደርሰዋል። ይህን የግፍ ሥርዓትና ሁኔታ፥
ኢሕአፓ ከቶም አልተቀበለም። ዛሬም አይቀበልም። ለብዙኃን ያልሆነች ኢትዮጵያ ለጥቂቶ
ች መሆን የለባትም ይላል። የማን ቤት ለምቶ የማን ሊጠፋም ባይ ነው። የሕዝብ መብት ባ
ልተከበረበት ሁኔታ፥ በሀገራችን ሠላምና መረጋጋት ይመጣል ማለት ዘበት ነው ይላል፥ ኢሕ
አፓ። ነገደ ሼራተኖች ብዙኃን አይደሉም ይላል። ለመንገድ አዳሪውና ለጎጆ ተኮራማች፥ለ
ሠርቶ አደሮ ሕዝብ ሰቆቃ ማብቃት-መወገድ ታጋይ ነው። በመሆኑም ከፀረ ሕዝቦችና ሆድ
አምላኪዎች ጋር የማይታረቅ ቅራኔ አለው።

ለኢሕአፓ ሕዝባዊነት ግንጥል ጌጥ ወይም ባዶ ቃል አይደለም። ዕምነቱ ነው። መመሪያ
ውና የትግሉ መሠረት ነው። ለኢሕአፓ፥ ኢትዮጵያዊነት፥ ኢሕአዴግ ነኝ ዓይነት ማደናገሪ
ያ ወያኔያዊ ባዶ ቃል አይደለም። እምነቱ ነው። ደሙን ያፈሰሰበት፤ መሥዋዕት የሆነለት
መርሁ ነው። ኢሕአፓ ሥልጣንና መብት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሲል ለማደናገርና ለማወናበድ
ሳይሆን፥ በእርግጥም ስለሚያምንበት ነው። በዚህ ሽፋን በልቡ ሥልጣን ለኢሕአፓ አመራ
ር ባይ ሆኖ በነበር፥ ከሰይጣኑም ከዲያብሎሱም አድሮ ለግሉ ሥልጣን ገና ድሮ በበቃ ነበር
። የኢሕአፓን ማንነትና ሀቀኛ አቋም ደግሞ እነማን ጠላቶቹ እንደሆኑ በመመርመር ልንደ
ርስበት እንችላለን። የቀድሞዎቹን ብንዘል፥ ዛሬ የኢሕአፓ ዋነኛ ጠላት፥ የመለስ ቡድን ነ
ው። ዛሬ ኢሕአፓ ላይ ወያኔን አጅበው ዘመቻ የከፈቱት በንፁህ ሕዝብ ደም የከረፉ፤ ሀገርን
የሸጡ፤ የግል ጥቅምና ሥልጣንን የሚያሳድዱ ወይም የወያኔ ቅጥረኞች ናቸው።እነዚህ የሀገ
ርና የሕዝብ ጠላቶች ሁሉ የሚረባረቡበት ድርጅት፥ በመሠረቱ ይዘቱና ትግሉ ለኢትዮጵያ
የሚበጅ ስለሆነ ነው። ባንዳ አርበኛን፤ ሌባ ፀረ ሌባን፤ ግብዝ ትሁትን፤ ከሀዲ ፀረ ክህደትን
ሊወድና ሊያወድስ ከቶም የሚጠበቅ አይደለምና ነው። የራዕዩ ግጭት መሠረቱም ይህ ነው፡
፡ የመለስ ቡድን ፀረ ሕዝብ ፀረ ኢትዮጵያ ነው። ኢሕአፓ ደግሞ ሕዝባዊና ኢትዮጵያዊ ነው
። በሁለቱ መሀል ገደሉ ሰፊ ነው። ድልድዩ ሊሰራ የሚችለውም ከሀዲው ወያኔ አቋሙን ሲ
ቀይርና ሕዝብን ይቅርታ ሲጠይቅ ነው። ይህ እስካልሆነ ድረስ ግን ፀረ ሕዝቡን የመለስ ቡድ
ን፥ ኢሕአፓ አምርሮ ይታገለዋል። ፀረ ሕዝቡ ስብስብም ኢሕአፓ ስሙ በተነሳ ቁጥር መቃ
ዠቱ ቀጣይ ይሆናል።

ይህ በነመለስ ዜናዊና በኢሕአፓ መካከል ያለው የቆየና ያመረቀዘ ልዩነት፥የግል ጠብ፥
የሁለቱ ድርጅቶች የሥልጣን ሹክቻ፥ የኃብት ሺሚያ፥ ወይም አንዳንድ ከንቱዎች እንደ
ሚሉት የዘር ጥላቻ ጭራሽ አልነበረም። አሁንም አይደለም። ልዩነቱ፥ የተነሳው፥ አሁንም
ያለው በመሠረታዊው የሀገራችን ዘላቂና ስትራተጂያዊ ጥቅሞች ላይ ነው። ይህ ልዩነት ደ
ግሞ ፥ ዘመን የማይሽረው ጊዜ የማይለውጠው ሆኗል። ኢሕአፓ ደግሞ፥ ይህ እስከ ሆነ ድረ
ስ በሀገራችን ዘላቂና መሠረታዊ ጥቅሞች ላይ መደራደር አይችልም-- አይቃጣውም። ያ
ከሆነ ዘንዳ፥ ያለው ምርጫ አንድ ብቻ ይሆናል። እርሱም፥ በዓላማው ፀንቶ መታገል ብቻ
ይሆናል። ለኢሕአፓ ደግሞ ይህ ዕንግዳ አይደለም። ይህንንም ውሳኔ ሲያደርግ፥ ከመጀመሪ
ያውም ቢሆን፥ ኃላፊነቱና ተጠያቂነቱ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ መሆኑን በሚገባ ስ
ለሚያውቅ ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ሉዕዋላዊነት ሳይከበር፥ የሕግ የበላይነት ሳይገኝ፥ ዲ
ሞክራሲያዊ ሥርዓት፥ ሌላው ቀርቶ፥ በጭላንጭል ደረጃ እንኳን ሳይከሰት፥ ኢሕአፓ በም

ንም ይሁን በምን ትግሉን ማቆም አይሆንለትም። ይህ መተከላዊ አቋሙ፥ ከመላው ኢትዮጵ ያ ሕዝብ ጋር በአያሌ ዕትብት ስላያየዘውና ብሎም የጀርባ አጥንቱ የጠነከረ ስለሆነ፥ ዓላማ ውና ራዕዩ ተጣጥመው ዕውን እስከሚሆኑለት ድረስ ትግሉን ይቀጥላል። የመለስ መንጋ ኢ ትዮጵያን ይጠላልና ኢሕአፓን ጠላት ብሎ ፈርጆ ማጥቃቱን ይቀጥላል። ሀቁ ይህ ነው። የ መጨረሻ አቸናፊ ግን ሕዝብና የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሚሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም።